


# ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጠንካራ ማህበረሰቦች ለመገንባት ከ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ጋር ይሥሩ

የኮሎምብያ ዲስትሪክ ለሰብዓዊ ሕይወት ከፍተኛ ክብር በመስጠት የሁሉም ነዋሪዎቹንና ጎብኚዎቹን ደህንነት መጠበቅ እና መከላከል የከተማ ፖሊስ መምሪያ (MPD) ተልዕኮ ነው። ስደተኛ ማህበረሰባችን የከተማችን ክፍል ዋነኛው አቋም ነው። MPD በማንኛውም ሁኔታ ላይ የሚገኙ ከሁሉም የስደተኛ ማህበረሰባችን ጋር በመነጋገር፣ እምነትን ማጎልበት፣ እና ደህንነታቸውንና ማህበረሰቡን በስፋት ለመጠበቅ በከፍተኛ ትጋት ይሠራል።

MPD ስለዜግነት ወይም የነዋሪነት ሁኔታን በመጠየቅ ግለሰቡ ህጋዊ ነዋሪ አለመሆኑን ለመገምገም ፖሊስ እንዳይጠይቅ የሚከለክል ለረጅም ጊዜ በሥራ ላይ የዋለ ፖሊሲ አለው።

የMPD ፖሊሲ አባላት የሚከተሉትን መጠየቅ እንደማይችሉ ይገልፃል፡

- ፖሊስ የህጋዊ ነዋሪነት ሁኔታን የተመለከተ የወንጀል ምርመራ (ለምሳሌ፣ የስደተኛ ከቦታ ወደቦታ ማንቀሳቀስ ወይም መደበቅ) በማካሄድ ላይ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንኛውንም ሰው ስለነዋሪነት ወይም የህጋዊ ነዋሪነት ሁኔታ፣ መጥየቅ
- የግለሰብን የህጋዊ ነዋሪነት ሁኔታ መረጃ ለማግኘት ብቻ በማንኛውንም ዓይነት የመረጃ ስብስብ በኩል መጠየቅ

MPD ወንጀልን ለመከላከል እና ለማስወገድ ከስደተኛ ማህበረሰቡ ጋር በጋራ ይሠራል። ዲስትሪክቱን ሰላማዊ የመኖሪያ፣ የሥራ እና የጨዋታ ቦታ ለማድረግ ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍል ወንጀልን ሪፖርት እንዲያደርግ እናበረታታለን።

DCPolice @DCPoliceDept OfficialDCPolice dcpolice dcpolicedept

**www.mpdc.dc.gov** Inquiries? Email mpd@dc.gov or call **(202) 727-9099**

METROPOLITAN POLICE WASHINGTON D.C.

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR